# ለምን ይዋሻል? እስከመቼስ ይዋሻል?

**ክፍል 4**

*የወያኔን ፓርላማ ምነዋ ንብ ሞላው?*
*ቀፎ በመሆኑ ነዋ!*

እየተባለ ያለው የወያኔን የዴሞክራሲና የፓርላማ ስርዓት ዋሾነት፤ ቧልትነትና ቀፎነት በሚገባ ይገልጠዋል። ለነገሩ ያለፉት ሁለት አገዛዞችም ፓርላማዎች ወይም ሸንጎዎች የይስሙላና የመጨ ዋቻ ወይም የመጦሪያ ተቋሞች እንጂ የዴሞክራሲያዊ ስርዓትና አገዛዝ ነፀብራቆች አልነበሩም። በሀሰት ላይ ተመስርተውና ሀሰትን መሰረት አድርገው የሚገዙ ሀይሎች ነበሩና፤ ናቸውናም ህብረ ተሰቡን በሀሰት ፕሮፓጋንዳ ናላውን እያዞሩ፤ ባዶ ተስፋን እየመገቡ፤ በቁስሉ ላይ ጨው እየነሰነሱ ቢቆዩም ፀረ ሕዝብነታቸውንና ውሸታምነታቸውን ምን ቢፍጨረጨሩ ሊሸፍኑ አቅቷቸው ተጋልጠዋል።

በኢሕአፓ ላይ  መጠነ ሰፊ ሀሰትና ውሸት ያሰራጨው ያለፈው አረመኔ ስርዓት ሲሆን ዛሬም የዚሁ ስርዓትና አገዛዝ ጋሻ ጃግሬዎች በወንጀላቸው ማፈርን ትተው እንዲያውም ኢሕአፓን ሊከሱ፤አዲስ ታሪክ ሊተርኩ፤ ጀግና ተባብለው ሊሸላለሙ ተነስተዋልና ያ ጊዜ ያለፈበት ውሸት ሁሉ ተህድሶ ተሰጥቶት በመናፈስ ላይ ነው። ነበረ፤ ትዝ አለን፤ምስክርነት እነሆ አቀረብን እያሉ ትላንት እርምጃ ይወሰድብት እያሉ ስንቱ የፖለቲካ እስረኛ ሰነድ ላይ እንዳልፈረሙ ሁሉ ዛሬም ዓይናቸውን በጨው አጥበው ሀሰትን በኢሕአፓ ላይ ያሰራጫሉ። የማያውቁትን ታሪክ አወቅን ብለው፤ ሀቅን አንቀው ገድለው በሬ ወለደ ውሸታቸውን በመፅሀፍ መልክ አሳትመው እንዲያሰራ ጩም ወያኔ ሙሉ ትብብርን ያደርግላቸዋል። ለነዚህ የሀሰት ጠራቂዎች በዝርዝር መልስ መስጠ ት ባንገደድም አልፎ አልፎ ግን በመደጋገሙ እውነት መስሎ እንዳይወሰድ ውሸትን ውሸት ብሎ ማጋለጥ የግድ ይሆናል።

ኢሕአፓ በሀገር ወዳድና ተራማጅ የኢትዮጵያ ልጆች የተመሰረተ ሆኖ ሳለ የሀሰት ዘማቾቹ ኢሕአፓ አንዴም በሻዕቢያ አሊያም በምዕራባውያን የስለላ ድርጅቶች ተመሰረተ ብለው ይዋሻሉ ። ሌሎች ደግሞ አዲስ ታሪክ በመፃፍና ራሳቸውን መስራችና አልፎም ያልነበሩትን የአመራር አባልነት ለራሳቸው ሰጥተው የሀሰት ትረካቸውን ሳያፍሩ ያስደምጣሉ። አባል ነበርን ልፈፋም ቀጥለው ለሚያቀርቡት ውሸት ማጠየቂያ ሆኖ ይገኛል። ነበረ ነበርን ለማለትና የራስን ውሸት እንደ ሀቅ ለማቅረብ ነው። በኢሕአፓ መስራች ጉባዔ ተገኝተው በአመራር ተመድበው ከነበሩት ዛሬ በህይወት ያሉ ሁለት ብቻ ሲሆኑ በድርጅቱ የቀጠለው ደግሞ አንድ ብቻ መሆኑ ሀቅ ነው። ስለዚህም የነመስራች ነበርን ጫጫታ የሀሰት ታሪክ መሆኑ ይጋለጣል።  ኢሕአፓ ተመስርቶ የሰራዊቱን እርሾ ሻዕቢያ ዘንድ ሳይሆን በፍልስጤሞች ዘንድ አሰልጥኖ ወደ ሀገር ሊያስገባ ሲነሳ በሶማሊያ በኩል ወደ ባሌ፤ በሱዳን በኩል ወደ ጎንደር ጎጃም መዝለቅ ባለመቻሉና ትግሉም

መጀመር ስለነበረበት ወደ ትግራይ ለመዝለቅ በመወሰኑ ከሻዕቢያ ጋር ግንኙነትን አደረገ ። ሻዕቢያም አንዱ ክፍል ሊተባበር ቢነሳም ሌላው ክፍል ደግሞ ኢሕአፓ የኤርትራን ቅኝ ግዛትነት ካልተቀበለ በሚል ንትርክ ጀምሮ ወደ ትግራይ መዝለቅ የነበረባቸው በዚያው በኤርትራ በረህ ለዓመት ያህል መቆየታቸው የግድ ሆነ። ሻዕቢያም በዚሁ ወቅት ወያኔን በማደራጀትና፤ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ብሎ በማስፈረምም የወያኔ ቡድን የኢሕአፓም ሀይል ቀድሞ ወደ ትግራይ እንዲዘልቅ አደረገው። የኤርትራ ግንባሮች ኢሕአፓን በወዳጅነት ሳይሆን በጠላትነትና ትምክህተኛነት ፈርጅው ሲያጠቁት ለመባጀታቸው ደግሞ ምስክር የሚጠይቀን ሊኖር አይችል ም። ኢሕአፓ መቸም ቢሆን ግን ታሪክን ክዶ ኤርትራ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ናት ብሎ አልፈረ መም። ችግሩ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ፤ አልፎም በተጨባጭ በፌዴሬሽን ትስስር ይፈታ አለ እንጂ።

ወያኔና የደርግ ታሪክ ሽምጣኞች በሞላ የአገዛዛቸውን መሰረታዊና ፀረ ሕዝብ ጥፋቶች ሁሉ በኢሕአፓ ላይ ለማላከክ መጣራቸው ያለና የቀጠለ ነው። አንዱ የደርግ ሻምበል ለምሳሌ ጀብሀ ለኢሕአፓ መሳሪያ ሲሰጥ፤ ኢሕአፓ ሶማሊያን ደግፎ በደርግ ጦር ላይ ሲተኩስ እንደነበር ወዘተ ፅፏል።  መንግስቱ የአዞ እንባውን እየረጨ ኢሕአፓ ዚያድ ባሬን ደገፈ ብሎ ጦሩን ያታለለበትና በግርግሩም ኢሕአፓ ላይ ዘመቻውን ያጧጧፈበትን ውሸት ሲያድስ ነው። የኢሕአፓ አባላት በተለይም በጦሩ ውስጥ የነበሩት ህይወታቸውን ለህገራቸው ሰጡ እንጂ ጠላትን ወዳጅ ብለው በወንድሞቻቻው ላይ አልተኮሱም። ኤርትራንም ያስገነጠሉት ችግሩን መፍታት ያቃታቸውና በፍጅትና ግድያ ለግንባሮቹ ደጋፊዎችን የሰጡት አገዛዞችና ግንባሮቹን የረዱት የባዕድ ሀይሎች እንጂ ኢሕአፓ አይደለም። ዛሬ ጀግና በሉን ባዮች የደርጉ መኮንኖችም አብዛኞቹ አረመኔው መንግስት መሪዎቻቸውን ሲገድል በዝምታ የተቀበሉና ጦሩንም መምራት አቅቷቸው ሽንፈትን የተከናነቡት ናቸው ተጠያቂ። ከሻዕቢያ  ዶላርን ተቀብለው ምስጢር እያሾለኩ ጦሩን ለሽንፈት የዳረጉ ኢሕአፓዎች ሳይሆኑ ከሀዲ ጀኔራሎች ነበሩ። መፈንቅለ መንግስት የሞከሩትን በግፍ የጨፈጨፉት የአገዛዙ ኮማንዶዎችና ወታደሮች እንጂ ኢሕአፓ አልነበረም። ደርጉም የሀገር ልጆችን በሽብር ጨፍጭፎና ሀገር ወዳድ መኮንኖችን ረሽኖ ሀገራዊ ሀይልን በማዳከሙ ለግንባሮ ቹ ድልና በአጠቃላይም ለጠባቦች መጠናከር ድልዳል አመቻችቷል። ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ ውሸትን መለፈፉ ምን ይጠቅማል? ሀገር ያሰረከበውን አገዛዝስ ጀግና ብሎ ለማወደስና ለመሸላለም ሠ መሯሯጥ ምን ይባላል?

ኢሕአፓ ህብረ ብሔራዊ ድርጅት ስለነበርም በአቅዋሙ ደረጃ በትምክህት ሆነ በጥበት ሊከሰስ የሚችል አልነበረም። ዛሬም ቢሆን ጠባቦችን ሁሉ በመታገል ላይ ነው። ትምክህት አንቋቸው በሕዝብ ላይ በጅምላ የሚያጓሩትንም በመታገል ላይ ነው--ፀረ ወያኔ ነን ቢሉም ለሕዝብ አንድነ ት ጠንቅ ናቸውና። በመሆኑም ኢሕአፓ የአማራዎች ድርጅት ነው ሲባል የከረመወና አሁንም በአንዳንድ ጠባቦች የሚስተጋባው ሀሰት መሆኑ ለማንም ግልፅ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ኢሕአ ፓ የትግሬዎች ወይም ኤርትራውያን ድርጅት ነበር ብለውም የሚዋሹትንም መጥቀስ ያስፈልጋ

ል። በብሄረሰብ ደረጃ ጠበው ያሉ ቡድኖች የኢሕአፓ ህብረ ብሄራዊነት ቢቆጠቁጣቸው የሚገር ም አይደለም። ኤርትራውያን በኢሕአፓ አባልነት ተሰልፈው ታግለው መስዋዕትነይን መክፈላቸ ው የኤርትራንም ግንባሮች ያስቆጣ፤ የኦጋዴን ተወላጆችም ኢሕአፓ ውስጥ አባል መሆናቸው ሶማሊያን ያበሳጨ፤ በርካታ አሮሞዎች ኢሕአፓ ሆነው መታጋለቸው ኦነግን ያበገነ መሆኑም የታወቀ ነው። በኢሕአፓ ውስጥ ከሁሉም ብሄረሰቦች የተዉጣጡ ታጋዮች ተሰልፈው ታሪክ ሰር ተዋል፤ እየታገሉም ናቸው። ሀገሬ ኢትዮጵያ ብሄረሰቤ ኢሕአፓ ብለው የታገሉ ናቸው ማለትም እንችላለን። ማን ከየት እንደመጣ እንደተወለደ ለኢሕአፓዎች ዋና ጥያቄ ሆኖ አያወቅም። ኢትዮጵያዊነትና ዴሞክራሲያዊነት--ሕዝባዊነት ነበር ዋናው ጉዳይ። አሁንም ቢሆን ይሄ ነው ዋናው ተፈላጊ እንጂ ውልደትና ብሄረሰብ ምንጭ አይደለም። ኢሕአፓ የኢትዮጵያ እንጂ የአንድ ብሄረሰብ ድርጅት አይደለም--እስቲ ሌሎች ይኸን ይበሉና ህቅ መሆኑ ይፈተሽ! የብሄረ ሰቦች እኩልነት ይረጋገጥ ስላለም አንድነትን ተፃረረ ሊሉ የሚፈልጉት ደግሞ ስለ አንደነትና መብት ከቶም የተረዱ አይደሉም። ስለዚህም የኢሕአፓን ሀገር ወዳድነትና ኢትዮጵያዊነት ማን ም ሊጠይቅ የሚችል ሀይል የለም። የኢሕአፓን ያህል ለሀገሩ አልተዋደቀምና።

ወያኔ ኢትዮጵያ ትገነጣጠል ብሎ ለግንጠላ የታገለና አሁንም ኢትዮጵያን እያደማና እያዳከመ ያለ ከሀዲ ሀይል ነው። የታወቀው ፀረ ኢትዮጵያ ስብሀት ነጋ በሶማሌ ወረራ ጊዜ ደርግ ላይ ተኩስ አቁመን ከጦሩ ጋር ልንሰለፍ ነበር ያለው ጭልጥ ያለ ውሸት መሆኑ ግልፅ ነው። ከግማሽ በላይ የኢትዮጵያን ምድር የሶማሊያ ነው ብሎ ፈርሞ በሞቃዲሾ ቢሮ ከፍቶ በሶማሊያ ይረዳ የነበረው ወያኔ የዚያድ ባሬ ጭፍን ደጋፊ መሆኑ የሚታወቅ ህቅ ነው። ዛሬ በየደርጅቱ የተኮለኮ ሉት ብዙዎቹ ደግሞ ኢትዮጵያን ካንበረከከው አረመኔ ኮለኔል ጋር ና ጎን ተሰልፈው ሕዝብን ሲያጠቁና ሀገርን ሲጎዱ የነበሩ ናቸውና ስለ ሀገር ወዳድነት ሊያወሱ አይችሉም። ቆመንለታል ላሉትም ብሄረሰብ የተዋደቁም አልነበሩም። አጋጣሚው ባመቻቸው ሁሉ ስልጣን ከያዘው ጋር እየተቃቀፉ ሕዘባችን ያሉትን የረሱ ነበሩ። ኢሕአፓ ከደርግም ሆነ ከወያኔም ጋር ተቃቅፎ ሕዝብን አልካደም። ማለትም ሀገርን ለጥቅም አሳልፎ አልሰጠም። ኢሕአፓ በአረመኔው የደርግ ሽብር ሲጠቃ የቀበሌና ከፍተኛ ታጣቂዎች ወይም የሽብሩ አራማጆች የነበሩ ዛሬ በየድርጅቱ ተሰግስገው ያን አሰቃቂና አሳፋሪ ታሪካቸውን በመደበቅ ውሸት የሚነዙት እነማን እንደሆኑ ሕዝብ ያውቃል። የደርግ ሹመኞች የነበሩ ኢሕአፓዎች የሉም-- ሕዝብን ክደው ከነበሩት ና ድርጅቱ ሊጠየቅባቸው ከማይችለው የአንጃ መንጋ ሌላ። ወያኔ ሲመጣም ኢሕአፓ ለግድያና ለእስር ተዳረገ እንጂ ፤ እነ ገብረ እግዚያብሔር (ጋይም) በአዲስ አባባ ተታኩሰው ተሰዉ እንጂ በወያኔ አልተሾመም ወይም ከሀገር የመውጫ ቪዛ ተሰጥቶት አባላቱን አስይዞ በአሳፋሪ መንገድ መሪዎቹን ከሀገር አላወጣም። ድርጅቱንና ሕዝብን ለወያኔ አሳልፈው ሊሰጡ የቃጡትንም አንጃ ብሎ አስወገደ እንጂ በርቱ አላላቸውም። ዛሬም ቢሆን መለስ ዜናዊ ኑ እንወያይ፤ ህገ ወያኔዬን ተቀበሉልኝ ሲል ጆሮ ሰጥተው ሕዝብን የሚክዱትን ያወግዛል እንጂ- ሂዱለት ኀበዞች አይልም። ማነው ኢትዮጵያዊ ታዲያ? ለሀገሩ የታገለና የተሰዋውና መከራን እየተቀበለ ያለው ወይስ ሀገሬ

ሀገሬ ብሎ በዘፈንና በማቅራራት ተወስኖ ሀገር ስትጣራ ጆሮውን ዘግቶ የግል ኑሮዎን የሚያመቻቸው? ኢትዮጵያዊነቱን የካደው? ሰብዐናውን ለባዕድ ቱጃር የሸጠውና ራሱን ያዋረደው? ሀቁ ሲታይ ግን ኢትዮጵያ ማነው የሞተልኝ ብትል  የቀድሞውና የዛሬው የባንዳ መንጋ ሳይሆን ስማቸው የሚጠራው የቀድሞ አርበኞችና በቅድሚያ ደግሞ የኢሕአፓ ነው::

ኢሕአፓ ሌሎች ድርጅቶችን ያጠቃል ተብሎም በሀሰት በድግግሞሽ ይቀርባል:: ቂመኛ ነውም ይባላል:: በመሰረቱ የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ ነውና ስንትና ስንት ሺ ጓዶቻችንና ሕዝብን የፈጁትን ልንፋረድ ብንነሳ ልንወቀስ አይገባም::  በጠላት ላይ ቂም መያዝና ጥላቻን መያዝ ተገቢናአስፈላጊም ነው--ጠላትን ወዳጅ ማለት ለውድቀትና ባርነት ዳራጊ ነውና:: ኢሕአፓ ግን ለሀገር ትግል አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ደግሞ ትላንት ካደሙትና ወንጀለኛ ብሎ ከፈረጃቸውም ጋር በጋራና ወቅታዊ ጠላት ላይ ለመረባረብ ሲል ብቻ አብሯቸው ለመሰለፍ ሞክሯል::  ያፈሰሱት ደም እያቃዣቸው በነሱው ብሶ ኢሕአፓን ሊያጠቁና ሊወጉ ወይም ለያዳክሙ ቢነሱም ቅሉ:: ጓዶቻችንን በአሲምባ የፈጀውና ያስፈጀው የወያኔ የቀድሞ መሪ ከወያኔ ተጣላሁ በማለቱ፤ የደርግ አመራር አባልና ሞትን ፈራጅ ዳኛ የነበረውንም ኮለኔል፤ በዘመናዊ ባንዳነት ተፈርጆ የነበረውና ስንቱን ወጣት በነፃ እርምጃ ያስፈጀውና የፈጀውን ቡድን የሚመራውንም ሳይቀር ለሀገር ጥቅም በሚል በግንባር ደረጃ ኢሕአፓ አቅፎ ሊታገል መሞከሩ የማይካድ ሀቅ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ዛሬ በየድርጅቱ የተሰገሰጉ ወንጀለኞች የሕዝብ ጎራ ለመቀላቀል ቢያንስ ንስሀ ይግቡ ብሎ መጠየቅ ሲያንስ ነው በሚልም ጥፋታችሁን እመኑ ፤ ሕዝብንም ይቅርታ ጠይቁ ብሎ ኢሕአፓ ትክክለኛና ተገቢውን አቅዋም ወስዷል::  ኢሕአፓ ደምቷል፤ተጠቅቷል፤ የሕዝብ ስቃይም ይሰማዋልና ሕዝብን የበደሉትን በዝምታ ካጨቀያቸው የንፁሀን ደም ጋር ሊያቅፋቸው አይቻለውም:: በዋናው ጠላት ላይ ማተኮር በሚል ዝም ቢላቸውም አልተዉትምና ዝም ሊላቸው አልቻለም:: የትላንት ወያኔዎች ማለትም ወያኔ ለስልጣን ሲበቃ የወያኔ ቁንጮ መሪዎች የነበሩና ሕዝብን የበደሉ፤ ጦርነት እንሰራባችኋለን ያሉን፤ በኢሕአፓ ላይ ጦርነት የከፈቱ፤ አባላቱን የገደሉና ደብዛቸውን ያጠፉ ዛሬ ዓይናቸውን በጨው አጥበው ያጠፋነው የለም፤ የምናውቀው የለም በሚልና ሁሉንም ጥፋት በመለስ ዜናዊ ላይ ብቻ ጥለው የሕዝብ መሪ በሉን ሲሉ ኢሕአፓ ይህን አሰቃቂ ሁኔታ ሊያስተናግድ ወይም በዝምታ ሊያልፈው አይችልም:: ዛሬ የሆነ ድርጅት መሪ ነን ስላሉ ብቻ ከበሬታ ሊሰጣቸው የሚችልና የሚገባ አይደለምና:: ቀይ ሽብር መካሄዱን የሚክድ የኢሠፓ መሪ የነበር ዶክተር ደግሞ የሆነ ድርጅት አባል ነውና ዛሬ ያን ቆሻሻ ታሪክ ሆነ ዛሬም ሽብሩን በመካድ የሚለፍፍውን በዝምታ አሳልፉት ሊባል የሚገባ አይደለም:: ብላንክ ቼክ ወይም ሙሉ ስልጣንን ሰጥተኖታልና ይፍጁት ሕዝብን ሲል መንግስቱን ይገፋፋ የነበር ይህ ዶክተር፤ የጓዳችንን ዓይን በሳንጃ ሊያጠፋ የሞከረና በባንዳነት ተሰልፎ አረመኔውን ደርግ ሲያገለግል የነበረ የዛሬ ፕሮፌሰር፤ መሳሪያ ይዛችኋልና ተጠቀሙበትብሎ ያሳሰበና ለሲቪል ሰልጣን እንዳይለቅ ደርጉን ይመክር የነበርና መለስን ልጄ ያለ ፕሮፌሰር ዛሬ የሆነ ድርጅት አባል ሆነዋልና ትግልን ሲያደፈርሱና ወደዱም ጠሉም በተጨባጭ ወያኔን ሲያግዙ በዝምታ እለፏቸውን ኢሕአፓ የሚሰማ አይደለም:: በሚባለው መንገድ ከተቀጠለ እኮ ነገ አረመኔውን መንግስቱን

ጀግና ብለው ሊሸልሙ የሚያቀብቁቡት ይሳካላቸዋል ማለት ነው:: ሕዝብ ጀግናውንና ወንጀለኛ ውን መለየት መቻል አለበት:: በግርግር ወንጀለኛን አገዛዝና ቁንጮዎቹን ጀግና ብሎ ለመሰየም የሚደረገው ርብርቦሽ በመሰረቱ ፀረ ሕዝብ አንቅስቃሴ ነው--ንስሀ ይቅደም፤ ሀቁ ይነገር! የትግል ና የሕዝብ ጎራ ወንጀለኞች የሚርመሰመሱበት ከሆነ ሕዝብ በዋነ ጠላቱ ላይ ድልን አያገኝም፤ ቢያገኝም ከሚወድቀው አገዛዝ የባሰ ሆኖ ሀገርና ሕዝብን ያስለቅሳል:: ስለዚህምኢሕአፓ የሕዝብ ትግል እንዳይጎዳና የጠራ እንዲሆን ፈለገ እንጂ ድርጅቶችን ለማጥቃት በሚል ተንቀሳቀሰ ማለት ሀሰትነው::

የዚህ ጉዳይ ሌላ ገፅታ ደግሞ ከዚህ በፊት ጣዖት አንጠርብምም አናስጠርብምም ያልነውን ይመለከታል:: ኢሕአፓ ስለ ድርጅትና የድርጅት መሪዎች ያለው ግንዛቤና አቅዋም ከሌሎች መለየቱ ሀቅ ነው:: ድርጅት ሕዝብን ለማገልገል፤ ለማታገል መሳሪያ ሆኖ መገኘት ያለበት እንጂ በሕዝብ ላይ የሚጫን አውቅልሃለሁ ባይ ጉድ ሊሆን አይገባውም ብሎ ያምናል:: የድርጅት መሪ ዎችም በፅናታቸው፤ ንቃታቸው፤ ቆራጥነታቸውና ችሎታቸው የተነሳ በቦታው ይመደባሉ እንጂ በድርጅትም በሕዝብም ላይ የሚኮፈሱ ሁሉን አዋቂ ሁሉን አዛዦች ግብዞች ሊሆኑ አይገባም ብሎ ኢሕአፓ ያምናል:: ሀውልት ይሰራልን፤ሁሉ ይንበርከከልን ጣዖቶች ሊሆኑም አይገባም ባይ ነው:: ስለዚህም የድርጅት መሪዎች ሲያጠፉ በአባሎቻቸውም ሆነ በሕዝብ ሊተቹ የሚገባቸው ናቸው እንጂ ስልጣናቸው የማይደፈር ወይም ከተተቹ ክብረ ነክ ወንጀል የሚሆን ከሆነ ድርጅቱ ችግር ውስጥ መግባቱ የማይቀር ነው:: ነውናም ኢሕአፓ ፈላጭ ቆራጭ የሚሆን አንድ ሊቀመን ብር በውስጡ አልሰየመም:: ለመሆን የቃጡትንም በአጭር አስቀርቶ ያው አንጃነታቸው ወይም በታኝነታቸው ማጥ ውስጥ ገብተዋል:: የድርጅት መሪዎችን በስራቸውና በፅናታቸው ማክበር ሲገባ በሌላ በኩል ተክለሰውነት ገንብቶ ጣዖት አድርጎ ማምለክ ደግሞ ድርጅትንም ትግልንም ይጎዳል:: ሀይማኖት ላላቸው ደግሞ አምልኮተ ባዕድ ይሆንባቸዋል--ከዚህ በፊት አንድ መሪን የጋንዲ፤ ማርቲን ሉተር ኪንግና የኢየሱስ ጥምረትና ነፀብራቅ ናቸው መባል ተደርሶ እንደነበር እናስታውሳለን::ነገርን በልክና በሚዛን መያዝ ብልህነት መሆኑ መረሳት የለበትም:: በሶቬየት ህብረት ስታሊን፤ በቻይና ማኦ ዜዱንግ፤ በኮሪያ ሟቹም ሆነ የአሁኑ ኪሞች በአፀያፊ ተክለሰውነ ትና ጣዖትነት  ዴሞክራሲን በፓርቲያቸው ውስጥም በሀገርም ደረጃ አጥፍተው የተቃወማቸውን ሁሉ ለማፈን እንደቻሉ ታሪክ መዝግቧል:: ኢሕአፓ ግን የጋራ አመራር ያለውና ማንም ግለሰብ እንደልቡ የማይፈነጭበት መሆኑንም ባለፉት 38 ዓመታት በሚገባ አስመስክሯል:: ሌሎች ድርጅ ቶች ግን በራሳቸው ላይ ቁንጮ ባለስልጣን መሪ ሰይመው--ወያኔም ሆነ ሻዕቢያን ማየቱም ይበቃ ል--ዴሞክራሲን በውስጣቸወም ሆነ በሀገር ደረጃ አጫጭተዋል፤ አጥፍተዋል:: ሀገር ወዳድ ድርጅቶችም የተባሉት እንዲሁ በመሪነት የሰየሟቸውን ግለሰቦች ወደ ጣዖትነት ደረጃ ለማድረስ እየፈለጉ በአቅዋም ደረጃ ትችት ሲደረግ መሪዎቻችን ተደፈሩ ብለው ቡራ ከረዩ ያሰማሉ:: ኢሕአፓ ግን ማንንም ድርጅት አልሰደበም--መተቸት ያለባቸውን ግን ተችቷል:: ትችትና ስድብ ደግሞ ለየቅል ናቸው::

ኢሕአፓ በራሱ ስምም ሆነ አባላቱ በፃፏቸው ፅሁፎች ማንንም ድርጅት ወይም መሪ አልሰደበም፡፡ ስድብ ማለት በአሁኑ ጊዜ በኢሕአፓና በመሪዎቹና አባሎቹ ላይ የሚካሄደው የስም ማጥፋት ርካሽ ዘመቻ ነው፡፡ ትችት ግን የተዛባና የተሳሳተ የፖለቲካ አቅዋሞችን ተንተርሶ የሚደረግ ሂስ ነው፡፡ ኢሕአፓ በሂስና ግለሂስ ያምናል--ይህን ልምድ እንደ አንዳንድ ድርጀቶች ራስን ሰድቦ ለሰዳቢ መስጠት ነው ብሎ አይወስደውም፡፡ የተቃዋሚ ድርጅት መሪ ጫማ በአንድ ደጋፊ በአደ ባባይ ሲሳም፤ የድርጅት መሪዎች አባላትን ሳያማክሩ ከገዢው ሀይል ጋር ሲፈራረሙ፤ ንብረት ሲባክን ሲታይ፤ ምስጢር በአደባባይ ሲሰጣ፤ አሰራር ሲጓደልና ትግልን ሲጎዳ፤ ምርጫው ላይ ማዕቀብ መደረግ ሲገባው በምርጫ ተሳትፎ ሲደረግ፤ ወዘተ ኢሕአፓ የመተቸት መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታም አለበት፡፡ አባላትና ሕዝብ ተስፋ ቆርጠው ከትግሉ እንዳይርቁ መታረም የሚገባ ነውናም፡፡ ኢሕአፓም በአቅዋሙ ና በተግባር ስህተት ከፈፀመ መተቸት አለበት፡፡ ሀሰቱን ሀሰት፤ የተሳሳተውን ተሳሳተ ይላል እንጂ የሹም ዶሮ ነኝ ማን ነክቶኝ ሊል አይችልም፡፡ ከዚህ ግንዛቤ ከተነሳን ድርጅቶች ሲተቹ ተሰደቡ የሚልን የሀሰት ክስ መደርደር ያከትማል፡፡ የበላይነትና ፍፁም ከበሬታ ሊሰጣቸው የሚገባ ሕዝብና ሀገር ናቸው፡፡ የድርጅት መሪዎች ሰዎች እንደመሆና ቸው መጠንና ትግሉም ገና ተጀመረ እንጂ የተገባደደ ባለመሆኑ ስህተት መፈፀማቸው የሚጠበቅ ነውና መተቸት አለባቸው፤ ይገባልም፡፡ አድሀሪ፤ አድርባይ፤ ፅንፈኛ፤ ጠባብና ትምክህተኛ ማለት ስድብ ሳይሆን የፖለቲካ አቅዋምን መግለፅ ነው፡፡ በቀድሞ ተማሪዎች ማህብር ብዙ የሀሳብ ፍጭት መካሄዱ ለጥራት ረዳ እንጂ አልጎዳም፡፡ በሀሳብ የተለያዩትም ተከባብረው ቀጥለዋል የዛሬ ዋሾዎች ሊሉ እንደቃጡት ነጋ ጠባ ሲደባደቡ አልነበረም፡፡ የጠራ አቅዋምና ግንዛቤን መያዝ በጣም አስፈላጊ መሆኑን የማይገነዘቡ የጥራዝ ነጠቅ ፖለቲካ አባወራዎች ግን የሀሳብ ፍጭት ተራ ንትርክና መሰዳደብ ይመስላቸዋል፡፡ ተራማጆች ያኔ ልዩነታቸው የማይታረቅ ደረጃ ሲደርስና በፖለቲካ ድርጅት ደረጃ መደራጀትም ሲከሰት መለያየታቸው የግድ ሆኗል፡፡ በዚህም መሰረት ኢሕአፓና መኢሶን ለምን በሰላም አልታገሉም የሚለው ትችት ውድቅ መሆኑ የሚታይ ነው፡፡ የመንግስት ስልጣንና የወደፊት የሀገሪቷን የፖለቲካ ዕጣ የሚመለከት ልዩነት ነበርና ማሽጋሸግ የሚቻል አልሆነም/አልነበረም፡፡ ያኔ ኢሕአፓና ወያኔ ሊግባቡ ያልቻሉት ዛሬ አንድ የወያኔ የቀድሞ መሪ እንደዋሸው በትግል ስልትና ቦታ ተለያይተው ሳይሆን በመሰረታዊ የህበረተሰቡ ቅራኔ አፈረጃጀት ላይ ተለያይተው ( ወያኔ የብሄረሰብ ቅራኔ ዋና ነውና ሁሉም ይገንጠሉ ባይ ነበር) ና ወያኔም ኢሕአፓን ከትግራይ መሬት ውጣ ስላለውና ጦርነትም ስለከፈተበት ነው፡፡ ዛሬም ቢሆን ወያኔን በሚደግፉ ተለጣፊዎችና ወያኔን ማስወገድ በሚሉ ሀገር ወዳድ ድርጅቶች መሀል መቻቻል ሊኖር አይችልም፡፡ የነበሩትን ቅራኔዎች በማባባስ ሌሎች ሀይሎች ሊጠቀሙ ቢጥሩም የቅራኔዎቹ መንስዔ ግድየለሽነት ወይም የፖለቲካ ብስለት ማጣት ሳይሆን የተቃረኑ አቅዋሞችን በመያዛቸው ምክንያት ነበር፡፡ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችና ለምሳሌ ኦነገ ሊተባባሩ ሳይችሉ የቆዩትም ኦነግ ኢትዮጵያዊ አይደለንም፤ ዓላማችን ተገንጥለን ነፃ ኦሮሚያን መመስረት ነው ስለሚል መሆኑ ይታያል፡፡ ሊታረቅ የሚችል አቅዋም አይደለም--ሊታረቅ የሚችለው ኦነግ አቅዋሙን ቀይሮ በኢትዮጵያ አንድነት ክልል ስር የኦሮሞን ሕዝብ መብት

እቀበላለሁ ካለ ብቻ ነው:: አሊያመ. ሀገረ. ወዳድ ሀይሎች የኦነግን ዓላማ ከተቀበሉ:: ይህን በተመለከተ ደግሞ ኢሕአፓ የኦነግን የመገንጠል አቅዋም ለኦሮሞ ሕዝብ የማይጠቅም ነው ሲል ሲተች ቆይቷል--ኦነግም ኢሕአፓን የሀበሻ ትምክህተኛ ሲለው ዘመን አልፏል:: ይህን ትችት በመሰንዘሩ ኢሕአፓ ኦነግን አልሰደበም ወይም የኦሮሞን ሕዝብ መብት አልተቃወመም፤አልተፃረ ረም:: ወደ ዝርዝሩ ከመጣን ደግሞ ከፀረ ኦሮሞ አገዛዞች ጋር አብሮ ተሿሚ ሆኖ የነበረው ኦነግ እንጂ ኢሕአፓ አልነበረም:: ስለዚህም ወደተነሳንበት ነጥብ ሰንመለስ ኢሕአፓ ትግሉን ቀና መንገድ ለማስያዝና የሕዝብን ጎራ ለማጠናከር ትችቶችን በግዴታ ደረጃ ሰነዘረ እንጂ ማንንም ድርጅት አልሰደበም ወይም ዘንድሮ ሊባል እንደተጀመረው አልነደፈም:: መንደፉን ንብ ነኝ ላለ ውና ለቆሸሸው ዝንብ ሀይል የተወለት ነወና:: ሂስና ትችትን መገደብ ደግሞ ጥራትንና ብሎም ጥንካሬን ማጥፋትና የግለሰቦችን አጓጉል የግል ክብር ከሀገርና ሕዝብ ጥቅም በፊት ማድረግ ነው:

ኢሕአፓ የባዕዳን ፍጡርና መሳሪያ ነው ብለው ሀቁን ገድለው ውሸትን ሊያነግሱ የሚጥሩት ሁሉ ፤ለሀገርና ለሕዝብ ብሎ የተነሳውንና በንቃቱም የተጠናከረውን ትውልድም የባዕዳን መሳሪያ ነበረ ብለው በሀሰት የሚወነጅሉ ሁሉ ራሳቸው የባዕድ መሳሪያና ቅጥረኛ መሆናቸው ሊጋለጥ የሚገባ ነው:: የአፄው አገዛዝ ሀገሪቷን ለአሜሪካ ሰጥቶ የአሜሪካ ወታደሮች በሀገር መሬት ሰፍረው ሠእንደልባቸው ሲፈነጩ ነበር:: ወደ ኮሪያና ወደ ኮንጎም የተደረገው ዘመቻ በመሰረቱ የምዕራባ ውያንን ጥቅም ለማስጠበቅ እንደነበርም ማንም አይዘነጋም:: በደርግ ዘመንም ሀገሪቷ ለሶቭየት ህብረትና አጋሮቿ ተሰጥታ እንደነበርም የምናውቀው ነው:: ወያኔም ለአረቦችና ለሶማሊያ፤ ለምዕ ራባውያንና ለሱዳን ያደረ ሀይል ሆኖ ቆይቶ ስልጣንን ከያዘም በኋላ ጭልጥ ብሎ በአሜሪካና እንግሊዝ ጫማ ስር ወድቆ ፤ ሀገርን በግንጠላ አዳክሞ፤ ሱዳን በሀገሪቷ እንዲፈነጭና መሬትም እንዲይዝፈቅዶ፤ ሕዝብን ለባዕዳን ጭፍንና ዘረኛ ብዝበዛ አጋልጦ፤ባዕዳንን ለማስደሰት ብቻ ዜጎች ን ወደ ሶማሊያ ልኮ አስፈጅቶ፤ በአፍሪካ ቀንድ የዘመናዊ ቅኝ ገዢዎች ተጠሪና አገልጋይ ሆኖ ያለነው:: ዛሬም ቢሆን ፀረ ወያኔ ነን እያሉ ግን የባዕዳን ሀይሎችን ጥቅም ለማስጠበቅ የተነሱ እንዳሉ ለሕዝብ ምስጢር አይደለም:: ኢሕአፓ ግን በዚህ ክህደት ሆነ ሀገርን አሳልፎ በመስጠት ወይም ለባዕዳን ተጎንብሶ ሀገርን በመጉዳት ከቶም ሊከሰስ የሚችል ሀይል አይደለም:: ሀቁ ከተነ ገረና ከታመነ--ውሸት ካልነገሰ፤ የፈጠራው ወሬ ካልሰፈነ ማለት ነው::

ታዲያ ምነዋ ውሸቱ ቢያከትምና ሁሉም ሀቅን ቢቀበል?

ይቀጥላል